# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT

مورو أ ريرحت ةهبجـــو

Gaafa: 06-04-2012 ibsa خيرات
Date:

Lakk.: 005/-abo/2012 مقر
No.:

## ***ሰሞኑ በኦነግ ስም ዋሽንግተን ፖስት ላይ የወጣው ዘገባ ጨርሶ ኦነግን ኣይመለከትም***

### ***የኦሮሞ ነፃነት ግንባር መግለጫ***

***የዋሽንግተን ፖስት ዘጋቢ ኤምሊይ ዋክስ ባለፈው ሚያዝያ* 1, 2012** “*As separatists in Ethiopia disarm, a new chapter for D.C.’s Oromo community*” ***በሚል ርእስ ኦነግ የራሱን ኣላማ ቀይሮ ኢትዮጵያዊነትን የተቀበለና የትጥቅ ትግሉንም እንዳቆመ በማስመሰል ከሃቅ የራቀ ዘገባ ማቅረቧ ይታወሳል። ይህ የሃሰት ዘገባ ለንባብ መብቃቱን ተከትሎ ፅሁፉን የማንበብ እድል ያገኙ የ ኦሮሞ ተወላጆች በሙሉ ከያሉበት የተቃውሞና የቁጣ ድምፃቸውን እያሰሙ ይገኛሉ።***

***የዘገባው ሃሰተኛነት የሚታየው የኦነግን የትግል ኣላማና ስልት ኣዛብቶ በማቅረቡ ብቻ ሳይሆን በሪፖርቱ ውስጥ በኦነግ ኣባልነት የተጠቀሱት ግለሰቦች ከቶውንም በኦሮሞ ነጻነት ግንባር ኣ ባላት ስም ዝርዝር ውስጥ የማይገኙ በመሆናቸውም ጭምር ነው። ዋሽንግተን ፖስት ስለ ድርጅ ታችን ትክክለኛ ሪፖርት ማጠናቀር ከፈለገ ኣሜሪካ ውስጥ በሚገኘው ቢሮኣችን ኣማካኝነት በቀጥታ ከቢሮው የስራ ሃላፊዎች ጋር በመገናኘት ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ይችል ነበር። ለዚህ እንዲረዳውም የኣሜሪካውን ቢሮኣችን የስልክ ቁጥሮች ከዋሽንግተን ዲሲ የቴሌፎን ማውጫ ዝርዝር ውስጥ እንዲሁም የቢሮውን የስራ ሃላፊዎች ስምና ኣድራሻ ደግሞ በኣሜሪካ የ ፍትህ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በኩል በቀላሉ ማግኘት ኣያዳግተውም ነበር። ይሁን እንጂ ይህንን ማድረግ እየቻለ ድርጅታችንን በሚቀናቀኑ ቡድኖች ተታልሎ የኦነግን ስም በእጅጉ ኣዛብቶ ለኣለም ማህበረሰብ በማቅረቡ በጣም እናዝናለን። የጋዜጣው ዘጋቢ ከጋዜጠኛነት ሞያዊ ስ ነምግባር ኣፈንግጣ ኣውቃም ይሁን ሳታውቀው ለፈፀመችው ስህተት እርማት እንድታደርግ ብትጠየቅም እስካሁን ይህንን ልታደርግ ኣልቻለችም ወይም ኣልፈቀደችም። ለኣንድ ወገን ብቻ በማዳላት የኦነግን ድርጅታዊ ሁኔታ ኣዛብታ በማቅረቧ በድርጅታችን ብቻ ሳይሆን በመላው የ ኦሮሞ ህዝብ ዘንድ እሷና ጋዜጣው ዋሽንግተን ፖስት ለትዝብት መዳረጋቸውን መሸሸግ ኣን ችልም።***

***የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ይህ የዋሽንግተን ፖስት ሃሰተኛ ሪፖርት ሊገልፀው እንደሚሞክረው የ ኦሮሞን ህዝብ ነፃነትና ሉኣላዊነት ለማረጋገጥ የመታገል ኣላማውን ኣልቀየረም። የተረገጡትን የ ህዝቡን መብቶች ሊያስመልስበት ያነሳውን ትጥቁንም ኣልፈታም፤ ትጥቅ እንዲያነሳ ያስገደዱት ሁኔታዎች እስከሚቀየሩ ድረስም ትጥቁን ኣይፈታም። የድርጅታችን ኣባላትና ደጋፊዎች፣ ሰፊው የኦሮሞ ህዝብ እንዲሁም የትግል ወዳጆቻችንና ኣለም ኣቀፉ ማህበረሰብ ይህንን እውነታ በግልፅ እንዲገነዘቡልን እንሻለን።***

***የግል ጥቅማቸውን ለማሟላት ሲሉ በኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ስትራቴጂኣዊ ጠላቶች ጉያ ውስጥ ተሸጉጠው እንዲህ ያለውን መሰረተ ቢስ ወሬ የሚነዙት ወገኖች እነማን እንደሆኑ ከ ህዝባችን የተሰወረ ኣይደለም። የኦሮሞ ህዝብ ፊቱን በነሳቸው ጊዜ ሁሉ ወደ ውጭ ሚድያ***

P. O. Box 6973 Asmara, Eritrea | Tel 2911 153848 | E-mail abamilki@gemel.com.er *www.oromoliberationfront.org*

ፊታቸውን በማዞር ሃሰተኛ ዘገባ ኣዘጋጅተው ተሰሚነት ሊያገኙበት መድከም ሁሌም የውድቀታቸውና የዝቅጠታቸው ምልክት ነው። በተመሳሳይ መልኩ ካሁን ቀደምም በደቡብ ኦሮምያ የሚንቀሳቀሰውን የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ኣሰፋፈር የሚመለከት ምስ ጢራዊ መረጃ ለኣንድ የውጭ ሚድያ ኣሳልፈው በመስጠት የወያኔ መንግስት በዚያ ሚድያ ኣማካኝነት ያገኘውን መረጃ ተጠቅሞ የዞኑን ሰራዊት እንዲያጠቃና ተስፋ ኣስ ቆርጦ እንዲማርክ እነዚህ ወገኖች ቅድመ ሁኔታዎችን ስለ ማመቻቸታቸው መላው የ ኦሮሞ ህዝብ ምስክር ነው። ዛሬም በኢትዮጵያ ኣንድነት ስም የሚንቀሳቀሱ ኣንዳንድ ሃይሎችና እነርሱን የተቀላቀሉ ገልቱዎች እውነተኛውንና ሃቀኛውን ኦነግ ለማሳጣት ሌት ተቀን ቢደክሙም በሁሉም መስክ ስላልተሳካላቸው በኦነግ ስም ራሱን የሚጠራ የ ጥቂት ሰዎች ስብስብ ጠፍጥፈው ዋሽንግተን ፖስት እንዲባርክላቸው በጥረት ላይ መሆናቸው የኣደባባይ ምስጢር ነው።

ይሁን እንጂ በኦነግ መሪነት እየተካሄደ የሚገኘው የኦሮሞ ህዝብ ትግል በጠላቶች የ ቀቢፀ ተስፋነት ጥረት ሳይደናቀፍ እስከ ግቡ ድረስ ይቀጥላል። እነ ዋሽንግተን ፖስ ትም ስለ ኦነግና የኦሮሞ ህዝብ ትግል ትክክለኛውን ምስልና ስኬት በተገቢው መልኩ በመዘገብ ዛሬ የሰሩትን ስህተት የሚያርሙበት ቀን ይመጣል።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር

ሚያዝያ 6, 2012